# የልዩ ፍላጎት/አካቶ/ ትምህርት ስትራቴጂ

**ትምህርት ሚኒስቴር**

**ሐምሌ 2004**

# የልዩ ፍላጎት/አካቶ/ ትምህርት ስትራቴጂ

**ትምህርት ሚኒስቴር**

**ሐምሌ 2004 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**መልዕክት**

ትምህርት እኩልነትን፣ መከባበርን፣ ዲሞክራሲያዊ ዕሴትንና ሰብዓዊ መብትን በማሳደግ በኩል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መሰረታዊ የሆነውን ሰብዓዊ መብት ከማስከበር ባሻገርም ድህነትን በመቀነስ ማህበራዊ ኑሮን ለማሳደግ የሚያበረክተው ድርሻ ቀላል አይደለም፡፡ ማንኛውም ዜጋ በህይወት ዘመኑ ለኑሮው መሻሻል በሚያደርገው ጥረት አጋዥ መሳሪያም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) ህገ መንግስት አንቀጽ 41 ማንኛውም ዜጋ በማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት እንዳለውና አካል ጉዳተኞችም አገልግሎቱን ሊያገኙ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 9(4) ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል መሆናቸውን በግልጽ ያስረዳል፡፡

የ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲያችን፤ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ጨምሮ ሁሉም ተማሪዎች እንደየችሎታቸውና እንደየፍላጎታቸው ሊማሩ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ፖሊሲ ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል የሃያ አመታት የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ቀርጾ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ከ1ኛውና ከ2ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ይልቅ ከትምህርት ገበታ ውጪ ለሆኑና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህጻናትና ወጣቶች በ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (1997 - 2002) ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በ1998 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ ቀርጾ ስራ ላይ ማዋሉ ይታወሳል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማትና ትምህርትን ለሁሉም ግቦች ለመምታት በምታደርገው ጥረት በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ቢሆንም ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህጻናት ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ አሁንም ብዙ ይቀራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ በአተገባበሩ ላይ ክፍተት ይታይበት ነበር፡፡ ስለሆነም የትምህርት ተደራሽነትንና ጥራትን ለማረጋገጥ የነበረውን ስትራቴጂ ከአዳዲስና ወቅታዊ አስተሳሰቦች ጋር በማጣጣም ማሻሻልና መከለስ አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም ራዕያችን በዕኩልነት ላይ የተመሰረተ አካታች የሆነ ስርዓትን በመገንባት የሰው ልጆች ሁሉ የተደላደለና በመከባበር ላይ ያተኮረ፣ ጤናማ የሆነ ኑሮ የሚኖሩባት ኢትዮጵያን ማየት ነውና ለዚህ ዕውን መሆን የተዘጋጀውን ይህን ስትራቴጂ በመተግበርም ሆነ በማስተግበር ሂደት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት የተባበረ ክንድ የሚጠይቅ በመሆኑ ከጎናችን እንድትቆሙ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

ደመቀ መኮንን

የትምህርት ሚኒስትር

ማውጫ

ገፅ

1. መግቢያ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 1

2. የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት------------------------------------------------------------------- ----- 2

3. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃ-ግብር ስትራቴጂና የስትራቴጂው አተገባበር
ግምገማ እንዲሁም ግምገማው በስትራቴጂው ክለሳ ላይ የሚኖረው አንድምታ--------------------- 4

3.1. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሀ ግብርስትራቴጂ ግምገማ------------------------- 4

3.1.1. ጠንካራ ጎኖች---------------------------------------------------------------------------------4

3.1.2. ደካማ ጎኖች----------------------------------------------------------------------------------4

3.2. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃ-ግብር ስትራቴጂ  አተገባበር ግምገማ--------------5

3.2.1. የተመዘገቡ ውጤቶች--------------------------------------------------------------------- 5

3.2.2. ደካማ ጎኖች-----------------------------------------------------------------------------------7

3.3. ግምገማው በሚከለሰው ስትራቴጂ ላይ የሚኖረው አንድምታ------------------------------------10

4. የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማዎች-------------------------------------------------------------------11

4.1. አጠቃላይ ዓላማ----------------------------------------------------------------------------------------11

4.2. ዝርዝር ዓላማዎች--------------------------------------------------------------------------------------11

5. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች----------------------------------------------------------------------------------------12

5.1. የትምህርት አመራሩንና አስተዳደሩን ማጠናከር-------------------------------------------------- 12

5.2. በሁሉም የትምህርትና ስልጠና ደረጃዎች ውስጥ ልዩ ፍላጎት ላላቸው
ህፃናት፣ወጣቶችና ጎልማሶች የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትን ማስፋፋት---------------------13

5.2.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማጠናከር----------------------------------------------------13

5.2.2. ምቹ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር--------------------------------------------------------------14

5.2.3. የአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ---------------------------15

5.2.4. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ
አካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችንና ተማሪዎችን የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትን ማሻሻል----15

5.3. አቅምን ማጎልበት----------------------------------------------------------------------------------------16

5.4. አካታች ስርዓት ትምህርትን ማራመድ-------------------------------------------------------------17

5.5. ውጤታማ የሆነ የድጋፍ መስጫ ስርዓት ማቋቋም------------------------------------------------20

5.6. በባለድርሻ አካላት መካከል አጋርነትን ማጠናከር------------------------------------------------24

5.7. ጥናትና ምርምር---------------------------------------------------------------------------------------- 25

5.8. ክትትልና ግምገማ-------------------------------------------------------------------------------------- 26

ተቀፅላ----------------------------------------------------------------------------------------------------- 28

## “የአካቶ ትምህርት የወደፊት አቅጣጫ”

**ጥራት ያለው አካቶ ትምህርት ሰብዓዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን እውን ለማድረግ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡**

48ኛው የዩኔስኮ የትምህርት ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ

ጄኔቫ፣ኖቨምበር 25-28, 2008(እ.አ.አ)

# 1. መግቢያ

ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ መሆን ያለበት መሰረታዊ - ሰብዓዊ መብት መሆኑ ዓለም ዐቀፍ ዕውቅና የተቸረው ጉዳይ ነው፡፡ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥም ድህነትን ለማጥፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማስመዝገብ ምትክ የሌለው ሚና እንደሚጫወት የታመነ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትም ይህን ዕውነታ በመገንዘብ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ጨምሮ ሁሉም ዜጎች ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት እንዳለባቸው በአገሪቱ ህገ መንግስትና በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ላይ በግልፅ በማስቀመጥ ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መንግስት፤ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የወጡ ዓለም ዐቀፍ ኮንቬንሽኖችን፤ ድንጋጌዎችንና፤ ስምምነቶችን በተለይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ2006 ያፀደቀውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽን ተቀብሎ በማፅደቅ ይበልጥ ቁርጠኝነቱን አሳይቷል፡፡

በዚህም መሰረት በተበታተነና ውስን በሆነ ደረጃ በአገሪቱ ለበርካታ ዓመታት ሲሰጥ የቆየውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስርዓት ባለውና በተጠናከረ ሁኔታ ለማካሄድ ይቻል ዘንድ ትምህርት ሚኒስቴር ህገ መንግስቱንና የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ በ1998 ዓ.ም አዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ ስትራቴጂውም አካቶ ትምህርትን በማስፋፋት የምዕተ ዓመቱን የልማትና የትምህርት ለሁሉም ግቦችን በማሳካት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ስትራቴጂው የተነደፈው ለአምስት ዓመታት (1998-2002 ዓ.ም.) እንዲያገለግል ታስቦ በመሆኑና የአገልግሎት ጊዜውን በመጨረሱ፣ ስትራቴጂው በራሱ መሰረታዊ የሆኑ ደካማ ጎኖች ስለነበሩትና በትግበራው ሂደትም ዐበይት ችግሮች በመከሰታቸው፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን ያፀደቀው ስትራቴጂው ከወጣ በኋላ በመሆኑና ትምህርት በባህርይው የማያቋርጥ የለውጥ ሂደት በመሆኑ ስትራቴጂውን ከአዳዲስና ወቅታዊ አስተሳሰቦች ጋር ለማጣጣምና የታዩ

ክፍተቶችን ለመሙላት ይቻል ዘንድ እንደገና ማሻሻልና መከለስ አስፈልጓል፡፡ ስለሆነም ይህ የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

ስትራቴጂው አራት ዋና ክፍሎችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ አካቶ ትምህርትን የማስፋፋት አስፈላጊነትን በአፅንዖት ያብራራል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የ1998ቱን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ እንዲሁም በትግበራ ወቅት የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮችን ከመገምገሙም ባሻገር ግምገማው በአዲሱ ስትራቴጂ ዝግጅት ላይ የሚኖረውን አንድምታ ያመላክታል፡፡ ሶስተኛው ክፍል የተሻሻለውን ስትራቴጂ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ሲያስቀምጥ አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ እነዚህን ዓላማዎች ዕውን ለማድረግ የሚረዱ የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ያመላክታል፡፡

ይህ ስትራቴጂ በአገር ዐቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ እንደመሆኑ የክልል/ የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ስትራቴጂውን ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ባለድርሻ አካላት እጅና ጓንት በመሆን ለስትራቴጂው ሙሉ ትግበራ በቁርጠኝነት እንዲሰሩ ትምህርት ሚኒስቴር ጥሪውን ያቀርባል፡፡

## 2. የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ በቁርጠኝነት በተቀበለቻቸው የምዕተ ዓመቱ ልማትና የትምህርት ለሁሉም ግቦች መርህ ውስጥ እንደተንፀባረቀው ትምህርት ሰብዓዊ መብት ነው፡፡
አገራችን አካል ጉዳተኞች በትምህርት ስርዓቱ በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ተካተው የመማር መብት እንዲላቸው ዕውቅና የሚሰጠውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2006 (እ.ኤ.አ.) የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን በ2002 ዓ.ም ተቀብላ አፅድቃለች፡፡ ይህ መብትም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9(4) መሰረት የአገሪቱ ህገ መንግስት አካል ሆኗል፡፡

አካቶ ትምህርት ዘርዘር ባለ መልክ ሲታይ፡-

- የተጠቃሚዎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻሉም ባሻገር ለራሳቸው ክብርና ዋጋ የመስጠት ስሜትን ያዳብሩ አምራች ዜጎችን ለማፍራት ያስችላል፤
- ለግለሰቦችም ሆነ ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያስገኛል፤

- መድልዎን በማጥፋትና ማህበራዊ ዕኩልነትን በማስፋፋት ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ለመፍጠር አስተዋፅዖ ያበረክታል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለማጠናቀቅና የትምህርት ለሁሉም ግቦችን ለመምታት ይረዳል፤
- በአገሪቱ ውስጥ ልዩ ትምህርት ቤቶችን ከማቋቋም ይልቅ ወጭ ቆጣቢና አዋጭ ነው፤
- ሁሉም ልጆች በትምህርት ቅስሞሽ (learning) ውስጥ ችሎታቸውን እንዲያውቁና እንዲያዳብሩ ይረዳል፤
- አካል ጉዳተኛ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ እንዲማሩ ያደርጋል።

ምንም እንኳን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አካል ጉዳተኞችና የመማር ችግሮች ያሉባቸው ህፃናትና ወጣቶች በአካቶ ትምህርት ስርዓት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድጋፍ እየተደረገላቸው ቢማሩም፤ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑትና ከፍተኛ ጉዳት (severe disability) ያሉባቸው ልጆች ማለትም የአካል (physical disability) ፤ የዓዕምሮ ዕድገት ውስንነት (intellectual disability) ፤ጥቂት የማይባሉ ኦቲስቲክ ልጆች (some autistic children) ፤መስማት-ማየት የተሳናቸው (deaf-blind) ፤ ወዘተ በልዩ ትምህርት ቤቶች (special schools) ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ልዩ ክፍሎች (special classes) ውስጥ ልዩ ስልጠና ባላቸው የትምህርት ባለሙያዎች የትምህርት አገልግሎት እንደሚሰጣቸው ሊታወቅ ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ አካቶ ትምህርት ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ልጆች የትምህርት ፍላጎት ለማርካት የሚረዱ ምቹ  የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ያስችላል።

## 3. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሀ-ግብር ስትራቴጂና የስትራቴጂው አተገባበር ግምገማ እንዲሁም ግምገማው በስትራቴጂው ክለሳ ላይ የሚኖረው አንድምታ

### 3.1. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሀ ግብር ስትራቴጂ ግምገማ፤

#### 3.1.1. ጠንካራ ጎኖች

- በአገሪቱ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን የወደፊት አቅጣጫ በግልፅ ያመላከተ የመጀመሪያው ሰነድ ነው፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት በአገሪቱ ለመተግበር የሚያስችሉ ቁልፍ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን አካቷል፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳዮች በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ውስጥ እንዲካተቱ ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፤
- የተለያዩ ባለድርሻዎች ልዩ ፍላጎት ስላላቸው ተማሪዎች ትምህርት ጉዳይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፤

#### 3.1.2. ደካማ ጎኖች

- በሁሉም ደረጃዎች ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ግልፅና በቂ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን አላስቀመጠም፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የበጀት አመዳደብን፤ በትምህርት ሚኒስቴር በተለያዩ የስራ ክፍሎች መካከል ስትራቴጂውን ለመተግበር አግድማዊ (horizontal) የስራ ግንኙነት አስፈላጊነትንና ፤በዞንና በወረዳ ደረጃዎች የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠሪዎችን ምደባ አስፈላጊነትን በግልፅ አላመላከተም፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለመፈተሽ የሚረዱ የምዘና መሳሪያዎች (screening and assessment tools) ዝግጅትና ትግበራን በተመለከተ ተገቢውን ትኩረት አልሰጠም፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ምዘናን አስፈላጊነትና የምዘና ዘዴዎችን አላካተተም፤

- ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸው ልጆች፤ ታዳጊዎችና ጎልማሶች የሚስተናገዱበት መንገድ አልተጠቆመም፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ጎልማሶች የሚስተናገዱበትን መንገድ አላመላከተም፤
- ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ አካባቢና ምቹ የትምህርት ግልጋሎቶችን ለመፍጠር የሚያስችል አቅጣጫ በግልፅ አላስቀመጠም፤
- አካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች በሴትነታቸውና በአካል ጉዳታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ድርብ ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አላመላከተም፤

## 3.2. የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃ ግብር ስትራቴጂ አተገባበር ግምገማ

### 3.2.1. የተመዘገቡ ውጤቶች

ስትራቴጂው በፈጠረው ምቹ ሁኔታ የሚከተሉት ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በመጀመሪያ ዲግሪ፤ ሁለተኛ ዲግሪና በፒኤችዲ ደረጃዎች፤ በባህር ዳር፤ በዲላ፤ በሃረማያና በጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ፤ እንዲሁም በአድዋ፤ በደብረብረሃን በኮተቤ፤ በጋምቤላ፤ በሆሳዕናና በሰበታ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች በዲፕሎማ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃ ግብሮች ተከፍተው በመስኩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ባለሙያዎች ሰልጥነዋል፤ አሁንም በመሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡

- በአገሪቱ በሚገኙ በሁሉም የመምህራን ትምህርት ተቋማት የልዩ ፍላጎት ትምህርት እንደ አንድ መሰረታዊ ኮርስ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን የትምህርት ክፍል በምልክት ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ስልጠና መሰጠት ተጀምሯል፡፡

- ትምህርት ሚኒስቴር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁለተኛ ደረጃ ለሚማሩ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች በፕላዝማ ፕሮግራም የምልክት ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

- በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ስራ ሊመሩና ሊያንቀሳቅሱ የሚችሉ ከየክልሉ ለተመረጡ የትምህርት ባለሙያዎች የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል፡፡
- በሳተላይት ወይም በአጎራባች ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት ድጋፍ እንዲሰጡ በአገር አቀፍ ደረጃ በናሙናነት በተመረጡ ስድስት የጉድኝት ትምህርት ቤቶች (cluster schools) እና ሶስት ልዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የድጋፍ መስጫ ማዕከላት የተቋቋሙ ሲሆን በነዚህም የድጋፍ መስጫ ማዕከላት ውስጥ የሚሰሩ አስር ተዘዋዋሪ መምህራን (ititnerant teachers) ተመድበዋል፡፡ ይህም በቀጣይነት ለሚሰሩ ስራዎች እንደ ሞዴል የሚያገለግል መነሻ ይሆናል፡፡
- በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ያሉትን የአመለካከት ችግሮች ለመቅረፍ የተለያዩ ዘመቻዎች የተካሄዱ ሲሆን ወደ ዘጠኝ ሺህ ለሚሆኑ የክልል፣ የከተማ፣ የዞንና የወረዳ ትምህርት ሃላፊዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡
- ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አሃዝ በአገር ዐቀፍ ደረጃ ማጠናቀር ጀምሯል፡፡
- የትምህርት ሚኒስቴር የ2003 ዓ.ም. ዓመታዊ የትምህርት ስታትስቲክስ መረጃ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 55,492 (ወ=32,072, ሴ= 23,420) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ እንደነበሩ ይገልፃል፣ ይህ ቁጥር በ1999 ዓ.ም. የትምህርት አገልግሎት ያገኙ ከነበሩት 33,300 (ወ = 19,561, ሴ =13,769) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር የ66.6 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በ2003 ዓ.ም. በአገሪቱ ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ብዛት 5,297 (ወ= 3,333, ሴ= 1,964) የደረሰ ሲሆን ይህ አሃዝ በ1999 ዓ.ም. ከነበረው 3,482 (ወ= 2,149, ሴ= 1,333) የሁለተኛ ደረጃ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጋር ሲነፃጸር የ52 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

3.2.2. ደካማ ጎኖች

- **በፈፃሚዎች በኩል የቁርጠኝነት ማነስ፤**

በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ላይ የሚገኙ አከናዋኞች የስትራቴጂውን ውጤታማ አተገባበር ለማሳለጥ የነበራቸው ቁርጠኝነት አናሳ ነበር፡፡ ለዚህም ዓይነተኛ መገለጫዎቹ በቸልተኝነት ሳቢያ፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠሪ አለመመደብ፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳዮችን በዕቅድ፤ በበጀት፤ በክትትል፤ በግምገማና በሪፖርት ውስጥ አለማካተታቸው ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

- **አግባብነት ያላቸው የመለያና የምዘና መሳሪያዎች አለመኖር፤**

የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮች ያለባቸው ማለትም የትኩረት ችግር ያለባቸው (attention deficit) ፤ የመቅበጥበጥ ችግር ያለባቸው (hypercative) ፤የመረዳትና የማስታወስ ችግር ያለባቸው (learning disability) ፤ ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ወዘተ ከጅምሩ ለመለየት (early identification) የሚያስችሉ የመለያና የምዘና መሳሪያዎች ባለመኖራቸው የተነሳ መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት ለመቀበልና ለማስተናገድ ሲቸገሩ ይስተዋላል፡፡

- **የአቅም ውስንነት**
    - በሁሉም የትምህርት እርከኖች ከፍተኛ የሆነ የልዩ ፍላጎት ትምህርትና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች እጥረት ይታያል፡፡
    - በመምህራን ትምህርትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመሰጠት ላይ ያሉት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ኮርሶች ልበ-ነቢባዊ (theoretical) ከመሆናቸውም ባሻገር በሜዲካል ሞዴል ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በዚህም ሳቢያ ምሩቃኑ የተግባር ክሂሎት ውስንነት ስላለባቸው በትምህርት ቤት ስራቸው ላይ ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

- **የግንዛቤ ውስንነት**

በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ውስን በመሆኑ አሁንም ቢሆን በሁሉም የትምህርት እርከኖች፤ በባለድርሻዎችና እንዲሁም በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የተዛባ አመለካከት በስፋት ይስተዋላል፡፡ በዚህም ምክንያት፡-

- በሁሉም ደረጃዎች ያሉ የፖለቲካ አመራሮች የስትራቴጂውን አተገባበር በቁርጠኝነትና ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ሊመሩት አልቻሉም፡፡

- o አብዛኛዎቹ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ለመቀበልና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡
- o አብዛኛው ማህበረሰብ በተለይም የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ወላጆች ማህበረሰቡ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ያለውን የተዛባና አሉታዊ አመለካከት ይጋራሉ፡፡ ይህ ወግ አጥባቂ አመለካከትና የዘልማድ እምነት የአካል ጉዳተኛ ህጻናት ወላጆች ልጆቻቸውን ከቤት እንዳያወጧቸው ያስገድዳቸዋል፡፡ አንዳንዴም ወላጆች ከአካል ጉዳተኛ ልጆቻቸው ጋር በመታየት ሀፍረት እንዳይሰማቸው በመስጋት ይደብቋቸዋል፡፡

- **ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚመደበው የትምህርት በጀት ውስን መሆን፤**

ለልዩ ፍላጎት ትምህርት የተመደበው በጀት አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የስትራቴጂው ትግበራ አፈፃፀም ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡

- **በቂ መረጃ አለመኖር**

በአጠቃላይ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን በተለይም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የሚመለከት በቂ መረጃ በአገሪቱ ውስጥ በቀላሉ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ያሉትም የትምህርት መረጃዎች ቢሆኑ የተበታተኑና በስርዓት ያልተደራጁ ናቸው፡፡ ለዚህም መንስዔ ከሆኑት ምክንያቶች ግንባር ቀደሙ አግባብነት ያላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አለመኖር ነው፡፡

- **የሚሰጠው የትምህርት አገልግሎት ውስን መሆን**
    - o ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትንና ወጣቶችን የሚያስተናግዱ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስን መሆንና በነዚህ በተወሰኑ ጥቂት ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚያገኙትም የተወሰኑ የአካል ጉዳት (ዓይነ ስውራን፤መስማት የተሳናቸው፤ የዓዕምሮ ዕድገት ውስንነት፤ የአካል እንቅስቃሴ ችግሮች ወዘተ ) ያለባቸው ህፃናትና ወጣቶች ብቻ መሆናቸው፤
    - o በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት የሚያገኙት አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ውስን

መሆንና ዕድሉን አግኝተው በመማር ላይ የሚገኙትም የሚያጋጥሟቸውን የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮች በራሳቸው ጥረት ብቻ የሚወጡ መሆኑ

- **የትምህርት ቤት አካባቢና ግልጋሎቶች ተደራሽና ምቹ አለመሆን፤**
  - ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ግልጋሎቶችን (ሽንት ቤት፤ ቤተ መፃህፍት፤ የግቢ ውስጥ አመላካች ሰሌዳ፤ መዝናኛ ስፍራዎች፤ መጫወቻ ቦታዎች፤ መንሸራተቻ (ramp)፤ ውሃ መጠጫ ቦታ፤ ወዘተ) ተደራሽ ለማድረግ የተወሰደ ርምጃ አልነበረም፤ እንዲሁም በቅርብ ጊዜ ከወጣው የህንፃ ግንባታ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 624/2001) በስተቀር የትምህርት ቤት ውስጥ ግንባታን ተደራሽነት ለማረጋገጥ የወጣ ደንብ አልነበረም፡፡
  - ከዚህ በተጨማሪ፤ ለአካል ጉዳተኞች መጓጓዣነት የተመቻቸ ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎት የለም፡፡

- **የመማሪያ -ማስተማሪያ ቁሳቁሶች፤ የጽህፈትና ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፤**

የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶች (በብሬል የተዘጋጀ የተማሪው መጽሀፍ፤ ጎላ ያሉ ፅሁፎች/ large print/፤ የሚዳሰሱ ስዕሎችና ካርታዎች፤ አባከስ /Abacus/፤ ወዘተ) ፤ የጽህፈት መሳሪያዎች ስሌት/slate/፤ ስታይለስ/styles/፤ የሚናገር ካልኩሌተር/Talking calculator/፤ የብሬል ወረቀት/Braille paper/፤ ወዘተ) ፤ ሌሎች መሳሪያዎች (የብሬል መጻህፍት ማዘጋጃ፤ ጃውስ /JAWS/ ኮምፒዩተር ሶፍትዌር ወዘተ) እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎች (ተሽከርካሪ ወንበር /Wheelchair/ ፤ ማዳመጫ መሳሪያ /Hearing aids/ ፤ ነጭ በትር /Cane/ ፤ ሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ መሳሪያ /Crutch/ ወዘተ) በአገር ውስጥ ገበያ ባለመገኘታቸው ትምህርት ቤቶች ግብዓቶችን ለማሟላትና አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ለመርዳት ሲቸገሩ ይስተዋላል፡፡

- **መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች አለመኖር፤**

በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፤ በከፍተኛ ትምህርትና በመምህራን ትምህርት ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ባለመኖራቸው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት አያገኙም፡፡

- **የስርዓተ ትምህርቱ ተለማጭ አለመሆን**
    - መምህራን መደበኛውን ስርዓተ ትምህርት ለእያንዳንዱ ተማሪ እንደየፍላጎቱ ለማስማማት የሚያስችላቸውን በቂ ስልጠና አልወሰዱም፡፡
    - በትምህርት ቤት ደረጃ ስርዓተ ትምህርቱን ለማስማማት የሚያስችል የአተገባበር መመሪያ የለም፡፡

ከላይ በተገለፁት የስትራቴጂው ትግበራ ደካማ ጎኖች ምክንያት ትምህርቱ ለአብዛኛዎቹ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ አልነበረም፡፡ ለምሳሌ በ2003 ዓ.ም. በአገር ዐቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አማካይ ጥቅል ተሳትፎ 96.4 በመቶ ሲሆን የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ግን 3.2 በመቶ ገደማ ብቻ ነበር፡፡* ይህም የሚያመለክተው ወደ 96.8 በመቶ የሚጠጉት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው ትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት መምህራኑ በልዩ ፍላጎት ትምህርት በቂ ስልጠና አለማግኘታቸው፤ የትምህርት ቤት ውስጥ ግልጋሎቶች አለመሟላትና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች አለመኖር ናቸው፡፡

### 3.3. ግምገማው በሚከለሰው ስትራቴጂ ላይ የሚኖረው አንድምታ

የ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂና የአተገባበሩ ግምገማ በሚከለሰው ስትራቴጂ ላይ የሚኖረው አንድምታ ሁለት ገፅታዎች አሉት፡፡ በአንድ በኩል፤ የሚከለሰው ስትራቴጂ በቀድሞው ስትራቴጂ ውስጥ ያልተካተቱትን ወይም በበቂ ሁኔታ ያልተገለፁትን ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች በተሟላ ሁኔታ መቅረብ እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቀድሞ ስትራቴጂ ትግበራ ወቅት ያጋጠሙትን ዋና ዋና ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ማካተት እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

*የተሳትፎ ምጣኔው የተሰላው ከአንድ ህዝብ ጠቅላላ ብዛት ውስጥ አካል ጉዳተኞች 10 በመቶ ድርሻ አላቸው የሚለውን የዓለም ጤና ድርጅት ግምት መሰረት በማድረግ ነው፡፡

# 4. የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ዓላማዎች

## 4.1. አጠቃላይ ዓላማ

የስትራቴጂው አጠቃላይ ዓላማ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ የአካቶ ትምህርት ስርዓትን በማጎልበት ጥራት፤ ተገቢነትና  ፍትሃዊ የሆነ ትምህርትና ስልጠና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሁሉም ህፃናት፤ ወጣቶችና ጎልማሶች ተደራሽ ማድረግና በሂደትም እነዚህን ዜጎች በአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ ነው፡፡

## 4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ስትራቴጂው የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ዕውን በማድረግ ላይ ያተኩራል፡

- አካል ጉዳተኛ ህፃናት፤ሴቶች፤ ወጣቶችና ጎልማሶች ከጉዳት አልባ አቻዎቻቸው እኩል የትምህርት ዕድል  ተካፋይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት በአካቶ ትምህርት ስርዓት የመማር መብት እንዳላቸው ለህብረተሰቡ ግንዛቤን በማስጨበጥ ትክክለኛ አመለካከት እንዲያዝና እነዚህ ህፃናት ተገቢውን የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በመምህራን ትምህርት ተቋማት የሚሰጠውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም በማጠናከር በሙያው በንድፈ ሃሳብና በተግባር ብቃት ያላቸው መምህራንንና ባለሙያዎችን ማፍራት፤
- በሁሉም የትምህርት ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ የድጋፍ መስጫ ስርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፤
- ስርዓተ ትምህርቱ የሁሉንም ልጆች ፍላጎት  በሚያስተናግድ መልኩ የማስማማት ተግባር በማከናወን እነዚህ ልጆች ተገቢውን ትምህርትና የሙያ (livelihood training) ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ናቸው፡፡

# 5. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

## 5.1. የትምህርት አመራሩንና አስተዳደሩን ማጠናከር

### ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

- የአካቶ ትምህርት አገልግሎቶች የሚተገበሩት ባለው የትምህርትና ስልጠና ስርዓት አደረጃጀት ውስጥ ነው፡፡ ስለሆነም፤ በትምህርት መዋቅሩ ውስጥ ባሉት የተለያዩ እርከኖች (ከትምህርት ሚኒስቴር አንስቶ እስከ አንድ የትምህርት ተቋም ድረስ) ያሉ አመራር አካላት ሁሉም ልጆች፤ ወጣቶችና ጎልማሶች የትምህርት ስርዓቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሙሉ ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠሪዎች በሁሉም የትምርት እርከኖች ማለትም በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲሁም በክልልና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ በዞን ትምህርት መምሪያዎችና በወረዳ ትም/ጽ/ቤቶች እንዲመደቡና የአካቶ ትምህርት ጉዳዮችን (ለትምህርት ቤቶች ሙያዊ ድጋፍ መስጠትን፤ ስልጠናዎችን ማደራጀትን፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎችን መረጃ በየታ ለይቶ መያዝን፤ የአካቶ ትምህርት እንቅስቃሴ በዕቅድ፤ በበጀት፤በግምገማና በሪፖርት አቀራረብ ውስጥ መካተቱን ወዘተ) በየተመደቡበት ደረጃ እንዲከታተሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### በቂ በጀት መመደብ

- ትምህርት ሚኒስቴር ለልዩ ፍላጎት/ ለአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ አስፈላጊውን በጀት ይመድባል፤
- ለልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደሮች በቂ በጀት መመደቡንና ለታለመለት ዓላማም ባግባቡ በስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርትን በመላ አገሪቱ በይበልጥ ለማስፋፋት ትምህርት ሚኒስቴር ከለጋሽ ድርጅቶች፤የልማት አጋሮችና ወዘተ ተጨማሪ ድጋፍ ያፈላልጋል፡፡

- የከፍተኛ ትምህርት እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በቂ በጀት በመመደብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
- በተመሳሳይ የክልልና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ የወረዳ ት/ጽ/ቤቶችና ት/ቤቶች ተጨማሪ ሀብት የሚገኝበትን ስልት ነድፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

**የትግበራ መመሪያና መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት**

- ትምህርት ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ስትራቴጂውን ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ ያዘጋጃል፤ የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ መመሪያውን ከአካባቢያቸውና ከተቋሞቻቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ትምህርት ሚኒስቴር ከክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በተለይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን መረጃ ለማጠናቀር የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡ እያንዳንዱ የትምህርት ተቋም፤ ክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮም ተገቢ የሆነውን መረጃ የማሰባሰብና ወደ ትምህርት ሚኒስቴር (EMIS) የመላክ ሃላፊነትና ተጠያቂነትም አለበት፡፡

## 5.2. በሁሉም የትምህርትና ስልጠና ደረጃዎች ውስጥ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት፤ወጣቶችና ጎልማሶች የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትን ማስፋፋት፤

### 5.2.1. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማጠናከር

አካቶ ትምህርትን ዕውን ለማድረግ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በመደበኛው የትምህርት ስርዓት ውስጥ መማር እንደሚችሉና በትምህርት ቤቱ ሀብትም (ለፍላጎታቸው መሟላት የሚበጀት ገንዘብን ጨምሮ) እኩል ተሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው አምኖ መቀበልን ግድ

ይላል። ይህንን ዕውነታ አምኖ አለመቀበል አካቶ ትምህርትን ዕውን ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከሚያጋጥሙት ዐበይት ተግዳሮቶች መካከል መሰረታዊው እንደሆነም መገንዘብ ያሻል።

ስለሆነም፤ ወላጆች፤ የአገር ሽማግሌዎች፤ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች፤ የትምህርት ዘርፍ አመራሮች፤ መምህራን፤ የአሰሪ መስሪያ ቤቶችና በአጠቃላይም ማህበረሰቡ በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ያላቸውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥ የተቀናጀና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማከናወን ያስፈልጋል።

ለዚህም ዘርፈ-ብዙና በዓላማ ላይ ያተኮሩ የተግባቦት (commuinication) አቀራረቦች ለምሳሌ (በዘመቻ መልክ፤ የማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር፤ በማህበራዊ ግብይት፤ ወዘተ) ፤ እንዲሁም፤ የተለያዩ ዘዴዎችን ማለትም (ዐውደ ጥናት፤ የቴሌቪዥንና ራዲዮ አጫጭር መልዕክቶች፤ የትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ፤ በራሪ ወረቀቶች፤ ማህበረሰብ ውይይቶች፤ የቡድን ውይይት፤ ሲምፖዚየም፤ ተለጣፊ ወረቀቶች፤ ወዘተ) መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያልተቆጠበ ተሳትፎ የሚጠይቅ ሲሆን በተለይም ትምህርት ሚኒስቴር፤ ከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ፤ የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ የዞን ትምህርት መምሪያዎችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ግንባር ቀደሙን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የተግባቦት መመሪያ (commuinication guideline) ተዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

### 5.2.2. ምቹ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር

#### ግልጋሎቶችን ተደራሽ ማድረግ

በአገራችን የሚገኙ አብዛኛዎቹ የትምህርት ተቋማት (ትምህርት ቤቶች፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፤ የመምህራን ትምህርትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የጎልማሶች ማስልጠኛ ጣቢያዎች) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ለማስተናገድ ምቹ አይደሉም። ስለሆነም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እንደ ሽንት ቤት፤ ቤተ መፃህፍት፤ የውሃ

መጠጫ ቦታ፤ መጫወቻ ስፍራዎች፤ በትምህርት ቤት ግቢ አቅጣጫ ጠቋሚዎች፤ ለተሽከርካሪ ወንበር ምቹ የሆነ መተላለፊያ ወዘተ በትምህርት ተቋማት ውስጥ ሊኖሩ ይገባል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ፎቆች ያለው ህንፃ ባሏቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን (learners with physical disabilities) የሚያስተናግዱ መወጣጫዎች (ramps) የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸት ተገቢ ነው፡፡ ለጊዜው ግን ምድር ቤት ባሉት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚስተናገዱበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ወደፊት ለመገንባት የሚታቀዱ ህንፃዎችም የአካል ጉዳተኛ ዜጎችን ባግባቡ ማስተናገድ ይችሉ ዘንድ ሀገራችን ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ባወጣችው የኢትዮጵያ የህንፃ  አዋጅ ቁጥር 624/2001 መሰረት የተሟላ አሳንሰር ወይም ለተሽከርካሪ ወንበር ምቹ የሆነ መወጣጫ  (ramp)እና ወዘተ እንዲኖራቸው ተደርገው መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

**ጓዳዊ የትምህርት አካባቢን መፍጠር**

በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና ጉዳት- አልባ አቻዎቻቸው፤ መምህራን፤ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞችና ድጋፍ ሰጪ አካላት መካከል ያለው ግንኙነት ጓዳዊ እንዲሆን በየደረጃው ያሉ የትምህርት ሃላፊዎች በተለይም ደግሞ የትምህርት ቤት አመራር አካላት ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስፋት ስራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 5.2.3. የአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ

አካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች በአካል ጉዳታቸውና በሴትነታቸው ምክንያት ድርብርብ ችግሮችና ተፅዕኖዎች ይደርስባቸዋል፡፡ ስለሆነም እነርሱን ወደ ትምህርት ቤትና ስልጠና ተቋማት ለማምጣትና  በቆይታቸውም ወቅት ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊው ማበረታቻና ልዩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

### 5.2.4. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችና ተማሪዎችን የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትን ማሻሻል፤

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ዕድሉን አግኝተው ከሚገቡት መካከልም በስልጠናው የሚሳተፉበት ሙያ መስክ

ከአንድ ወይም ሁለት ዓይነት አይበልጥም፡፡ ስለሆነም፤ እነዚህ ሰልጣኞች በስልጠናው ዘርፍ በስፋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አበረታች የሆነ የመመልመያ መስፈርት (affirmative admission) ይነደፋል፡፡

ከዚህም ባሻገር፤ የትኞቹ የስልጠና ዓይነቶች ለየትኞቹ አካል ጉዳተኞች ተስማሚ እንደሚሆኑ፤ በስልጠና ወቅትም ሊደረጉ የሚገባቸው እገዛዎች ምን ምንን ያካትታሉ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስችል ዘንድ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎችና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎችና ኤጀንሲዎች በተናጠልና በጋራ የጥናትና ምርምር ስራ ሊያካሂዱበት ይገባል፡፡ ከስልጠናው ባሻገርም በስራ ስምሪት ወቅት ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር ከወዲሁ ለመቅረፍ የጥናትና ምርምሩ ስራ አቅጣጫ አመላካች እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ዘርፈ ብዙ የሆኑ ችግሮች እንዳሉባቸው ተረድተው ተቋማቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሰልጣኞችና ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት የሚያስችላቸውን ስትራቴጂ ያዘጋጃሉ፡፡

## 5.3. አቅምን ማጎልበት

### የመምህራን ስልጠና

አካቶ ትምህርትን ለመተግበር ዓይነተኛውን ሚና የሚጫወቱት መምህራን ቢሆኑም ሌሎች ባለሙያዎችም በተለይም የምክር አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርት ቤት አስተዳደር አካላትና የመምህራን አሰልጣኞች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡

ስለሆነም ሁሉም መምህራን (የቅድመ -መደበኛ ትምህርት መምህራንን ጨምሮ) ብዝሀ-ፍላጎቶችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ አዎንታዊ አመለካከቶችን፤ እሴቶችንና ክሂሎትን ሊታጠቁ ይገባል፡፡ ይህም ዝግጅት በመምህራን ልማት ፕሮግራም ስር በሚከናወነው የመምህራን ቅድመ-ስራ ስልጠናና የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራሞች አማካኝነት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ አካል ጉዳተኛ ጎልማሶችን ለማገዝም፤ ለአመቻቾች በሚሰጡ የቅድመ-ስራና የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራሞች ውስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት መሰረታዊ ጉዳዮች እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

ከዚህም አንፃር ትምህርት ሚኒስቴር አሰልጣኝ መምህራን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ጉብኝት በማድረግ ልምድ እንዲቀስሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

**ድጋፍ ሰጪዎችን፤ በልዩ ፍላጎት የተለያዩ ባለሙያዎችንና የትምህርት አስተዳደር ኃላፊዎችን ማሰልጠን**

የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ትግበራን ማጠናከር ይቻል ዘንድ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤በክልልና በከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች እንዲሁም ለሌሎች የትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ፤ ተዘዋዋሪ መምህራንና በድጋፍ መስጫ ማዕከላት ለሚሰሩ ባለሙያዎች ቅድመ ስራና የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራሞች ይመቻቻሉ፡፡ ስልጠናውም ባለሙያዎቹ የአካል ጉዳት ዓይነቶችን በመለየት ተገቢውን እገዛ መስጠት እንዲችሉ የሚረዳ ከመሆኑ ባሻገር ከትምህርት ተቋማት አመራርና መምህራን ጋር በመሆን የአማካሪነት ሚናቸውን እንዲጫወቱ ያግዛቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የተለያየ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎች ለምሳሌ የንግግር ወጌሻ (speech therapist) የአካል ወጌሻ (physiotherapist) ወዘተ ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም ባለሙያዎች በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ በአገር ውስጥ የሚሰለጥኑበት ስርዓት እንዲዘረጋ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የትምህርት ቤት አመራሮችና ሱፐርቫይዘሮችም በስራቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ብዝሀ- ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢውን እገዛ እንዲሰጡና የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ትግበራ እንዲያጠናክሩ የሚያስችላቸውን ክሂሎት እንዲታጠቁ ይደረጋል፡፡

**የአሰልጣኝ መምህራንን አቅም መገንባት**

ከላይ ለተገለፁት ባለሙያዎች ውጤታማ ስልጠና ለመስጠት በመምህራን ትምህርት ተቋማት ለሚያስተምሩ መምህራን የትምህርት ደረጃና ክሂሎት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ የአሰልጣኝ መምህራኑ የትምህርት ደረጃ ዝቅተኛ ከሆነና የክሂሎት ማነስ የሚታይባቸው ከሆነ በስልጠና የማብቃትና ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም አንፃር ትምህርት ሚኒስቴር በመምህራን ትምህርትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች

የሚሰጡ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት የስልጠና መርሀ-ግብሮች ከአካቶ ትምህርት ፍልስፍና ጋር ተጣጥመው እንዲዘጋጁ ጥረት ያደርጋል፡፡

## 5.4. አካታች ስርዓተ ትምህርትን ማራመድ

**ስርዓተ ትምህርቱን ማስማማት** (adapting curriculum)

አካታች ስርዓተ ትምህርትን አዘጋጅቶ በተግባር ለመተርጎም በዓለም አቀፍ ሰነዶች ተለይተው የተቀመጡትን የአካታች ስርዓተ ትምህርት ባህርያትን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ባህርያት ስርዓተ ትምህርቱን ተለማጭ፤ ተገቢና፤ከዕድሜ ልክ ትምህርት ተከታታዮች፤ ብዝሀ-ፍላጎቶችና ባህርያት ጋር ማጣጣምን (adjustability) ያካትታል፡፡

በአካታች ክፍል ውስጥ በአብዛኛው ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ ሁለት ወይም ሶስት ደረጃዎች ላይ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ በዕድሜ ደረጃቸው የሚማሩ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ዓመት ቀድመው የሚማሩ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው ደረጃ በታች ዝቅ ብለው የሚማሩ ናቸው፡፡

ይህም መምህራን በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎችን ለማስተማር የሚያስችሉ ዘርፈ-ብዙ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው፤ ወይም ቢያንስ በክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል የትምህርት አቀባበል ልዩነቶች መኖራቸውን ዐውቀው ትምህርቱን ማስማማት እንደሚገባቸው ያሳያል፡፡ የማስማማቱ ስራ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው ፈጥነው የሚማሩትንና ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ያካትታል፡፡

ስርዓተ ትምህርትን የማስማማት ስራ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚተገበር ሲሆን ትምህርት ሚኒስቴር ፤ ከፍተኛ ትምህርት፤ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የስርዓተ ትምህርት ማስማሚያ የትግበራ መመሪያ ያዘጋጃሉ፡፡

**የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ድዘና (Designing Individual Education Program)**

የአንዳንድ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ሁኔታ የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ-ግብር እንዲታቀድላቸው ያስገድዳል፡፡ ስለሆነም መምህራን እነዚህን ተማሪዎች ለማስተናገድ የነፍስ-

ወከፍ ትምህርት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለመተግበር ያግዝ ዘንድ የባለሙያዎችና የመምህራን አቅም እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ በሁሉም የእርከን ደረጃዎች ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል በፌዴራል ደረጃ የአተገባበር መመሪያ ይዘጋጃል፡፡ በመመሪያው ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል፤ በተዋረድም አተገባበሩን የመከታተልና ሙያዊ ድጋፍ የማከናወን ስራ ይካሄዳል፡፡

**ተስማሚ የመማሪያ- ማስተማሪያ ቁሳቁሶችንና የፅህፈት መሳሪያዎችን ማቅረብ**

በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተስማሚ የሆኑ የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን (በብሬል የተዘጋጀ መፅሀፍ፤ ጎላ ያሉ ፅሁፎች፤ የሚዳሰሱ ስዕሎችና ካርታዎች፤ አባከስ፤ ወዘተ) እና የፅህፈት መሳሪያዎችን (ስሌት፤ ስታይለስ፤ የሚናገር ካልኩሌተር፤ የብሬል ወረቀት፤ ጃውስ (JAWS) የኮምፒዩተር ሶፍትዌር፤ ወዘተ) ቢያንስ በትምህርት ስታንዳርድ የተቀመጠውን አነስተኛውን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፤ ከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፤ የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር እነዚህ ቁሳቁሶችና የፅህፈት መሳሪያዎች በአገር ውስጥ ገበያ በቀላሉ የሚገኙበትን መንገድም ያፈላልጋሉ፡፡

**የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና (Learning Assessment) ስርዓትን ማሻሻል**

በትምህርት ቤት የሚሰጥ ምዘና ተማሪዎችን በደረጃ ለማስቀመጥ ወይም ለመምረጥ የምንጠቀምበት ከሆነ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ዝቅተኛውን ውጤት ማስመዝገባቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ እነርሱን እንደ ወዳቂ ስለሚያስቆጥራቸውና ከሌሎች ተማሪዎች ስለሚያገላቸው ለመማር አያተጋቸውም፡፡ ስለምዘና ስናነሳ መዘንጋት የሌለበት ነገር ቢኖር፤ የምዘና ዋነኛ ዓላማ የትምህርት ቅስሞሽን በማመቻቸትና የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን በመምራት የትምህርት ዓላማዎችን ማሳካት እንጂ ተማሪዎችን ለይቶና መርጦ ወደ ሚቀጥለው ክፍል ማሳለፍ ብቻ አለመሆኑ ነው፡፡ ምዘናው ተማሪው የሚያውቀውን፤ በተግባር የሚሰራውንና ያካበተውን ልምዱን ማሳየት መቻል አለበት፡፡

ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ምዘና ሲሰጥ የምዘናው ዘዴዎች የተማሪዎችንና የሰልጣኞችን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች (አካል ጉዳት፤ ባህርይ፤ ወዘተ) ግምት ውስጥ ማስገባት

አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፤ ዓይነ ስውር ተማሪ/ሰልጣኝ ምዘና ሲሰጠው በቃል፤ በብሬል ተፅፎ፤ ወይም በቴፕ ሪከርደር ተቀርፆ ሊሰጠውና በተግባር ሊፈተን ይችላል፡፡ መስማት የተሳነው ተማሪ/ሰልጣኝ ምዘና የቀለም ወይም የተግባር ሊሆንና በምልክት ቋንቋ ሊደገፍ ይገባል፡፡ እንዲሁም የመማር ችግር ያለበት ተማሪ/ሰልጣኝ ተጨማሪ ሰዓት ሊያስፈልገው ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፤ ተማሪው ባለበት ችግር ምክንያት በቀን አንድ ፈተና ብቻ ሊወስድ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንደ ፖርትፎሊዮ፤ የፕሮጀክት ስራ፤ ግለ-ምዘና፤ ምልከታ፤ የመሳሰሉት የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች  የፈተና ተጨማሪ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ እንደ አማራጭ ሆነው ሊያገለግሉ ይገባል፡፡ ለዝርዝር አፈፃፀሙ በየትምህርት እርከኖች የተለያዩ መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡

### ተግባር-ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን ለአካል ጉዳተኛ ጎልማሶች ተስማሚ ማድረግ

በጎልማሶች ተግባር -ተኮር ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ክለሳ ወቅት የአካል ጉዳተኛ ጎልማሶች የትምህርት ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ አመቻቾችም በስልጠና ወቅት የቀሰሙትን ዕውቀትና ክሂሎት በመጠቀም ለአካል ጉዳተኛ ተሳታፊዎች አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያዎች መሰረታዊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ማለትም እንደ ስሌት፤ ስታይለስ፤ የምልክት ቋንቋ መዝገበ ቃላት፤ አባከስ ወዘተ የመሳሰሉትን የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ መደበኛ ያልሆነ የሙያ ስልጠና ለነዚህ ጎልማሶች ቢሰጣቸው አምራች ሃይል በመሆን ራሳቸውንና አገራቸውንም ይጠቅማሉ፡፡ በጎልማሶች ትምህርት ውስጥ አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የሚያመቻች የአፈፃፀም መመሪያ ይዘጋጃል፡፡

## 5.5. ውጤታማ የሆነ የድጋፍ መስጫ ስርዓት መዘርጋት

የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች፤በየደረጃው ለሚገኙ የክፍል መምህራንና ለትምህርት ተቋማት አመራር አካላት መሰጠት ይኖርበታል፡፡ ይህም የድጋፍ አሰጣጥ የተለያዩ ቅርፆች ያሉት ሲሆን የሚከተሉትን አቅርቦቶች ይጨምራል፡፡

- ለመምህራንና ለአሰልጣኞች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- ምቹ ሆነው የተዘጋጁ የመምህሩና የአሰልጣኙ መምሪያዎች ዝግጅት፤
- ምቹ ሆነው የተዘጋጁ ተገቢ የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች፤
- የልዩ ክፍሎች ወይም ዩኒቶች መኖር፤
- የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ተዘዋዋሪ /ተንቀሳቃሽ መምህራን፤
- በክፍል ውስጥ መደበኛ መምህራንንና አሰልጣኞችን የሚያግዙ ረዳት መምህራንና አሰልጣኞች መኖርና በቅንጅት ማስተማር፤
- ለትምህርት አመራሩ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት (በመረጃ አሰባሰብ፤ በሪፖርት አዘገጃጀት፤ የፍላጎት ደሰሳ ጥናት ወዘተ) ናቸው፡፡

**የመለያና የምዘና መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም**

ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍ ለመስጠት በተቻለ መጠን በትምህርት ቤት ህይወታቸው መጀመሪያ (በቅድመ መደበኛና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት) ፍላጎታቸውን መለየትና መመዘን ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ዕውን ለማድረግም መምህራን በክፍላቸው ውስጥ በምልከታና የመለያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን መለየት የሚያስችላቸው ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ በመነሻ ምዘናዎች ችግር እንዳለባቸው የተለዩ ተማሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ ችግራቸውን በጥልቀት ለመዳሰስ ልዩ ስልጠና ወደ ወሰደ ባለሙያ (ተዘዋዋሪ መምህር) ሊላኩ ይችላሉ፡፡ ይህን ለማድረግም የተማሪዎቹን ወላጆች በቅድሚያ ማማከር ያስፈልጋል፡፡

በአገሪቱ ውስጥ በስራ ላይ የዋለው የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያው እርከን የንባብ ምዘና መሳሪያ (Early Grade Reading Assesmnet) በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎችን ለመለየት የሚያስችል መሰረት ጥሏል፡፡ ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች በሂሳብ ትምህርት ያሉባቸውን ችግሮች ለመለየት ይቻል ዘንድ የሂሳብ የምዘና መሳሪያም ተዘጋጅቷል፡፡ በቅድመ-መደበኛ የሚማሩ ህፃናትም ያሉባቸውን ችግሮች ለመለየት የሚያገለግል

መሳሪያም በትምህርት ሚኒስቴር ይዘጋጃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናትና ወጣቶች ለመለየት የሚያስችሉ የመለያ መሳሪያዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሁሉም መምህራንና አሰልጣኞች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወላጆች ጭምር የተወሰነ ስልጠና በመውሰድ ለመለየተ የሚያስችላቸው የመማር ችግር ያለባቸውን ልጆች የመለያ መሳሪያ ይዘጋጃል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ደረጃ ከፍ ያሉና በባለሙያዎች አማካይነት የጉዳት ዓይነትንና መጠንን መለየት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ተገቢው የማስተዋወቂያና የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፡፡ ሙያው የሚመለከታቸው አካላትና ሴክተር መስሪያ ቤቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበት ስርዓትም ይዘረጋል፡፡

**ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን (Resource Centers) በቁሳቁሶችና በሰው ሃይል ማጠናከር**

በተጓዳኝ ትምህርት ቤቶችና በልዩ ትምህርት ቤቶች የሚገኙና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች የሞንቴሴሪ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (በተለይ ለመጀመሪያ ደረጃ) ፤ ቴሌቪዥን፤ ዲቪዲና ቪዲዮ፤ ካሜራ፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች(wheel chairs) ፤ ነጭ በትር (cane)፤ ማድመጫ መሳሪያዎች (hearing aids)፤ በከፊል ማየት ለተሳናቸው የሚያገለግሉ የዕይታ መነፅሮች፤ የሰው ሰራሽ አካል መረማመጃ (crutch)፤ ወዘተ እና በተለያዩ ባለሙያዎች (የስነልቦና ምሁራን፤ የብሬል አሰልጣኞች (ለመጀመሪያ ደረጃ) ፤ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ወዘተ በማሟላት በጉድኝት ፤ በሳተላይትና አጎራባች ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና መምህራን አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፤ በመምህራን ትምህርትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት በተመሳሳይ መልኩ እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በ2ኛ ደረጃና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚገኙ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በማገዝ ዙሪያ አትኩሮት ሲያደርጉ፤ በመምህራንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ማዕከላት ደግሞ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሰልጣኞችን ለማፍራት የሚያስችሉ የምርጥ ተሞክሮ ማዕከላት(center of excellence) ሆነው የሚያገለግሉና በስራቸው ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እገዛ የሚያደርጉ ይሆናሉ፡፡ ቀደም ሲል የድጋፍ መስጫ ማዕከላት

ባልተቋቋመባቸው ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ተቋማት ውስጥም ማዕከላቱ እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡

እንዲሁም፤ የድጋፍ መስጫ ማዕከላት በአቅራቢያቸው በሚገኙ የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያዎች ለሚሳተፉ አካል ጉዳተኛ ጎልማሶችና አመቻቾች አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃና በ2ኛ ደረጃ የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን የማሰልጠንም ሆነ የመመደብ ኃላፊነት የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎችና የወረዳ ትም/ ጽ/ቤቶች ሲሆን፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፤ በመምህራንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን የማሰልጠንና የመመደብ ኃላፊነት የተቋማቱ ይሆናል፡፡

### በልዩ ትም/ ቤቶችና ልዩ ክፍሎች ለሚገኙ መምህራን የማትጊያ (Incentive) ስርዓት መዘርጋት

ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች (learners with severe disabilities) ትምህርታቸውን የሚከታተሉት በልዩ ትምህርት ቤቶችና በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ በልዩ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ለእነዚህ ልጆች የትምህርት እገዛ ለማድረግ የሚጠይቀው ጥረት እጅግ ፈታኝና አድካሚ ነው፡፡ በመሆኑም በነዚህ ልዩ ትምህርት ቤቶችና ልዩ የመማሪያ ክፍሎች ተመድበው በማገልገል ላይ የሚገኙ መምህራንን ለማትጋትና ሙያቸውን አፍቅረው እንዲቀጥሉበት ለማበረታታት ከመደበኛ ደመወዛቸው በተጨማሪ ማትጊያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለዚህም የሚረዳ የአፈፃፀም መመሪያ ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጃል፡፡

### የወላጆችንና የአቻ ለአቻ ድጋፍን ማሳደግ

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ እንደሰፈረው ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ተገቢውን እገዛ ከአቻዎቻቸው እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችንና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ያካተተ “የአካል ጉዳተኛ ክበብ” በማቋቋም በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና ጉዳት-አልባ በሆኑ አቻዎቻቸው መካከል በዕኩልነት፤ በመከባበርና እርስ በርስ በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ

ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ወላጆችም ልጆቻቸውን በማስተማርና በመደገፍ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ፤ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ወላጆች ልጆቻቸውን በማገዝና ተገቢውን መረጃ በመስጠት የማይናቅ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ፡፡ የልጆቻቸውን የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ-ግብር በመንደፍና በመተግበር ሂደትም የትምህርት ተቋማቱ ተጨማሪ አጋዥ ኃይል ናቸው፡፡ በመሆኑም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ወላጆች በትምህርት ቤትና በተቋማት ደረጃ በሚቋቋመው የወላጅ-መምህራን- ተማሪዎች ህብረት ወይም በሌላ አደረጃጀት ውስጥ በአባልነት እንዲካተቱ ማድረግ ይገባል፡፡ ለአፈፃፀም የሚረዳ መመሪያም ይዘጋጃል፡፡

## 5.6. በባለድርሻ አካላት መካከል አጋርነትን ማጠናከር

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ማለትም አጋር ድርጅቶች፤ መሰረተ-ማህበረሰብ ተሀድሶ (Community Based Rehabilitation) አከናዋኞች፤ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበራት ፌዴሬሽን፤ የአካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበራት፤ የግል የትምህርት ተቋማት፤ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፤ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር) ኃላፊነት ነው፡፡ ስለሆነም ከነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረና የተቀናጀ የስራ ግንኙነት በመፍጠር መስራት ይጠበቃል፡፡

### አማካሪ ኮሚቴዎችን ማቋቋም

በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አፈፃፀም ዙሪያ ለትምህርት ሚኒስቴር ተገቢውን የምክር አገልግሎት የሚሰጥና ስትራቴጂውን በመቅረፅ፤ በመተግበር፤ በመገምገምና አስፈላጊውን የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ በማሰባሰብ ለታለመለት ተግባር ማዋል ይቻል ዘንድ በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ግንኙነት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለመተግበር የአካቶ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴዎች በአገር ዐቀፍና በክልልና ከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡

## በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ባሉ የተለያዩ የስራ ክፍሎች መካከል ያለውን የስራ ትብብር ማጠናከር

የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት አቀራረብ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀባይነትን ማግኘት፤ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አካል የሆኑ ኤጀንሲዎችና ማዕከላት እንዲሁም በስሩ የሚገኙ የተለያዩ የስራ ክፍሎች/ዳይሬክቶሬቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎችንና ሰልጣኞችን ትምህርት ጉዳይ በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩ ግድ ይላቸዋል፡፡

በነዚህ አካላትና የስራ ክፍሎች ትብብር የሚከናወኑ ተግባራት ልዩ ፍላጎት ባላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ትምህርት ዙሪያ መረጃ ማሰባሰብ፤ የስርዓተ ትምህርት ማስማሚያና የነፍስ-ወከፍ ትምህርት መርሀ-ግብር መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ውስጥ አካቶ ትምህርትን ለመተግበር የሚያስችል ማኑዋል ማዘጋጀት፤ በቋንቋና የሂሳብ ትምህርቶች የመለያና የምዘና መሳሪያዎች ማዘጋጀትና የመሳሰሉትን ያካትታሉ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር እንደ አንድ ተቋም በዚህ ሰነድ ውስጥ የተቀመጡት ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ስራ ላይ መዋላቸውን  የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 5.7. ጥናትና ምርምር

በዚህ ሰነድ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ እንደተገለፀው፤ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የመረጃ ክፍተቶች በስፋት ይታያሉ (ለምሳሌ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች ብዛት፤ አካቶ ትምህርትን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ንቁ ሚና የሚጫወቱ ባለሙያዎች ቁጥርና ከፍተኛ ስልጠና ወስደው ስለተቀጠሩ ባለሙያዎች ብዛትና የመሳሰሉት መረጃዎች በተሟላ መልኩ አይገኙም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ትምህርት ሚኒስቴር በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ማለትም በአካታች ክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ስትራቴጂዎች፤ ስርዓተ ትምህርትን ማስማማት፤ የምዘና መሳሪያዎችና አጠቃቀማቸው፤ ከትምህርት ቤት ውጪ ስላሉ ልጆች፤ ስለዝቅተኛ ውጤት አስመዝጋቢዎች፤ ስለ ትምህርት ቤት አቋራጮች፤ ስለክፍል ደጋሚዎች፤ የድጋፍ መስጫ ማዕከላት አሰራር፤ በትምህርት አመራር አካላት ዘንድ የአመለካከት ለውጦችን ስለማምጣት  ስለመምህራንና

ወላጆች፣ በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የስልጠና ዕድል ስለማሳደግ፣ ስለ ህንፃዎች ምቹነትና ተደራሽነት፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የቅጥር ዕድል ማስፋትና በመሳሰሉት ርዕሶች ዙሪያ ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄዱ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህም ጋር በተያያዘ በትምህርት ሚኒስቴር በተለይም የአካቶ ትምህርት የሚመለከተው ክፍልና ጥናትና ምርምሩን በሚሰሩ አካላት በተለይም በመምህራንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጥብቅ የስራ ግንኙነትና ትብብር መኖሩ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡

በተጨማሪም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችና ሰልጣኞች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተለያዩ ተግዳሮቶች ስለሚጋጥሟቸው እነዚህን የትምህርት ቅስሞሽ እንቅፋቶች ለመቅረፍ መምህራንና አሰልጣኞች ተግባራዊ ጥናትና ምርምር (action research) እንዲያካሂዱ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 5.8. ክትትልና ግምገማ

የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን በፌዴራል ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በክልል፣ በወረዳና በት/ቤትደረጃ፣ ተከታታይ ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡ በክትትልና ግምገማ ሂደት ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች ክፍተቶችን ለመለየት ከማገዛቸው ባሻገር እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ ግብረ- መልስና ቴክኒካዊ ድጋፍ ለመስጠት ያስችላሉ፡፡ ይህንንም የክትትልና ግምገማ ተግባራት አፈፃጸም ትምህርት ሚኒስቴር ያስተባብራል፡፡ ለክትትልና ግምገማ ስራ የሚውሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ቼክ ሊስቶችንና የሪፖርት ቅፃችንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና በተለይም ከከፍተኛና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚመለከታቸው አካላትና ተቋማት እንዲሁም ከክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ ስራ ላይ እንዲውሉም ያደርጋል፡፡

በፌዴራልና በክልል ደረጃዎች የተዋቀሩት አማካሪ ኮሚቴዎች ትምህርት ሚኒስቴርና የክልል የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች በሚያደራጁት የክትትልና ግምገማ ቡድኖች ውስጥ ተወካይ ይኖራቸዋል፡፡

በተለያዩ ደረጃዎች የሚዘጋጁት የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ወቅታዊ ሪፖርቶች በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ እየተሰራበት ባለው የሪፖርት አቀራረብ ውስጥ ተካተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳይ በወረዳ፤ በክልልና በፌዴራል ደረጃ (በአጠቃላይ፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት) በሚካሄዱ የትምህርት ጉባዔዎች ትኩረት ተሰጥቶትና እንደ አንድ አጀንዳ ተይዞ ለውይይት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

## ተቀፅላ

### የቁልፍ ቃላት ትርጉም

1. **ልዩ ትምህርት** (Special Education)

   ልዩ ትምህርት ለአካል ጉዳተኞችና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ወዘተ ያሉባቸው ተማሪዎች በልዩ የመማሪያ ክፍሎች፤ በዩኒቶችና በልዩ ትምህርት ቤቶች በተለየ መልኩ ለማገዝ የሚደረግ የትምህርት አደረጃጀትን ያጠቃልላል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶችም ሆነ የመማሪያ ክፍሎች የሚያስተምሩ መምህራንም እነዚህን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ለመርዳት የተለየ ስልጠና የወሰዱ ሲሆን ተማሪዎችም የተለያዩ ባለሙያዎችን እንደ ቴራፒስቶች የመሳሰሉትን የመነብኘት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የተማሪ- መምህር ጥምርታውም ከመደበኛው ትምህርት ያነሰ ነው፡፡

2. **ልዩ ፍላጎት ትምህርት** (Special Needs Education)

   ልዩ ፍላጎት በመሰረቱ ልዩ ትምህርትን ተክቶ የመጣ አደረጃጀት እንጂ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ፅንሰ- ሃሳቦች አይደሉም፡፡ ይልቁንም፤ ለአካል ጉዳተኞችም ሆነ የማህበራዊና ስሜታዊ ችግር ያሉባቸውን ጨምሮ የመማር ችገሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡ ይህም በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ የመማሪያ ክፍሎች ከሚሰጡ የትምህርት ድጋፎች ጀምሮ በማካተት የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡

3. **ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች** ( Learners with Special Educational Needs)

   ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የምንላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ የመማር ችግሮች የሚያጋጥማቸውንና በዚህም ሳቢያ የአጭርና የረዥም ጊዜ ተጨማሪ ድጋፍን የሚሹ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን፤ በሌላ አገላለፅ እነዚህ ተማሪዎች የመማርና የዕድገት እንቅፋቶች የተጋረጡባቸው ልጆች ናቸው፡፡ እነዚህን ተማሪዎች የጥቅም ተጋሪ እንዳይሆኑና ከትምህርቱ እንዲገለሉ የሚያደርጓቸው በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ በጥቂቱ ለመጥቀስም፤

- አካል ጉዳተኝነት፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች
- ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ
- የማህበራዊና አኮኖሚያዊ ዝቅተኝነትና ተያይዞ የሚመጡ የተመጣጠኑ ምግብ እጥረቶች
- ኤችአይቪ ኤድስ
- ውህዳን ብሄረሰብ/ ባህላዊ ተፅዕኖ
- ብቸኝነትን የተላበሰ ገጠራማ ኑሮ
- የተለያዩ ጦርነቶችና ግጭቶች ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ምንም እንኳን በሰነዱ ላይ የተጠቀሱት መርሆዎች ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ሰለባ የሆኑትን ልጆች በሙሉ የሚያጠቃልል ቢሆንም፤ ዋነኛ ትኩረቱ በአሁኑ ሰዓት ከትምህርት ገበታ ውጭ በሆኑና በርካታ ቁጥር ባላቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ተጠቂ በሆኑት ተማሪዎች ዙሪያ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ የሚገባው ጉዳይ ከላይ ከተገለፁት ችግሮች አንዱ በሌላኛው ችግር ላይ በተደራቢነት በመከሰት ተማሪውን የጣምራ ችግር ሰለባ ሊያደርገው እንደሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ከአካል ጉዳተኝነት በተጨማሪ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ዝቅተኝነት ሳቢያ በብቸኝነትና በገጠራማ አካባቢ ለመኖር የመገደድ አጋጣሚ በተማሪው ላይ ሊፈጠር ይችላልና፡፡

4. **አካቶ ትምህርት** (Inclusive Education)

በዩኔስኮ (እ.ኤ.አ. 2005) አገላለፅ “አካቶ ትምህርት የትምህርት ስርዓቱን በማጎልበት ትምህርትን ለሁሉም ልጆች ለማዳረስ የሚደረግ ሂደት ነው…” እንደ አጠቃላይ መርህ ሁሉንም የትምህርት ፖሊሲዎችን ተግባራት በመምራት ትምህርት መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት መሆኑንና የበለጠ ፍትሃዊና በዕኩልነት የተመሰረተ ህብረተሰብ ለመፍጠር መሰረት በመጣል ይጀምራል፡፡ ስለዚህም አካቶ ትምህርት በድህነት፤ በስርዓተ ፆታ፤ በዘር፤ በቋንቋ ወይም በአካል ጉዳት ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ተማሪዎች የማስተናገድ ዝግጁ የሆነ የትምህርት ስርዓት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

አካቶ ትምህርት ሁሉም ልጆችና ተማሪዎች ሊማሩ ይችላሉ ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ የትምህርት አቀራረብ በትምህርት ቤቶች ፣ በሙያ ማሰልጠኛ፣ በከፍተኛ ትምህርት፣ በመምህራን ትምህርትና በትምህርት ቤት የትምህርት አመራር ውስጥ የትምህርት ቅስሞሽ እንቅፋቶችን መለየትና እነዚህን እንቅፋቶች መቀነስ ወይም ማስወገድ አስፈላጊና የማይታለፍ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ አካቶ ትምህርት ለመገለልና ዝቅተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ትኩረት ይሰጣል፡፡ በዚህ የትምህርት አሰጣጥ የትምህርት አካባቢው የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ለማስተናገድ መስማማት እንደሚኖርበት ግድ ይላል፡፡ ይህም ማለት፣ ምቹ የመማሪያ አካባቢ ካለና ድጋፍ ከተደረገላቸው ሁሉም ልጆች ይማራሉ የሚለውን የአካቶ ትምህርት መሰረታዊ ግምት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም በትምህርት ቤቱና በስርዓቱ ላይ ሁሉንም ልጆች በሚያስተናግድ መልኩ ተግባራዊ ለውጥ ለማምጣት ማለትም በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አመለካከት፣ በማስተማር ዘዴዎች ማስማማት፣ በትምህርት ግብዓቶች አቅርቦት፣ በስርዓተ ትምህርት ማስማማት፣ የትምህርት ቤቱን አካባቢና ግልጋሎቶችን ተደራሽ ማድረግን ያመላክታል፡፡

5. **መቀላቀል** (Integration)

በአካቶ ትምህርት አቀራረብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመደበኛው ክፍል ውስጥ ሲሆን በመቀላቀል አቀራረብ ግን እነዚህ ተማሪዎች በመደበኛው ክፍሎች ውስጥ እንዲማሩ ለሙሉ ቀን ወይም ለግማሽ ቀን (ለተወሰነ ጊዜ) ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በቀሪው የትምህርት ጊዜያቸው በልዩ ክፍል ወይም ዩኒት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ አገሮች መቀላቀልን የአካቶ ትምህርት ሙሉ ትግበራ ከመካሄዱ በፊት እንደ ሽግግር ወቅት ይጠቀሙበታል፡፡

6. **ተዘዋዋሪ/ ተንቀሳቃሽ መምህር** (Itinerant Teacher)

ተዘዋዋሪ መምህር በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተመረቀ ባለሙያ ሲሆን ለመደበኛ መምህራን ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ለወላጆች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የሚሰጠውም አገልግሎት የተማሪውን የነፍስ -ወከፍ የትምህርት መርሀ-ግብር ትግበራን፣ የተማሪውን የትምህርት ፍላጎት ምዘናን ከሳተላይትና ከጎረቤት ትምህርት

ቤቶች ርዕሳነ-መምህራንና መምህራን ጋር ትብብር መፍጠርን ፤ የልጁን የትምህርት ግቦች ለመምታት ሌሎች ባለሙያዎችንና ወጌሻዎችን በማስተባበር፤ በተማከለ ቡድን (core team) ተግባራት ውስጥ መሳተፍንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

7. **የድጋፍ መስጫ ማዕከል**(Resource center)

የድጋፍ መስጫ ማዕከል ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች መገልገያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን፤ የአካል ድጋፍ መስጫ መሳሪያዎችንና ለሁሉም ተማሪዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የያዘ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ማዕከል ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች፤ ለመደበኛ መምህራንና ለጎረቤት ትም/ ቤቶች ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይይዛል፡፡